# <u>የኢኮቴ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት</u>

## ራዕይ፣

የህዝባችንን ህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማሻሻል በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚፈጠሩትን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም በዞናችን ቀጣይነት ያለው ማኀበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሰፍኖ ማየት

## ተልዕኮ፣

በዞናችን የልማት እንቅስቃሴ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን በማጐልበት የዞናችንን ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበለጸገ እንዲሆን ማድረግ

## እሴቶች

- መረጃ ሀብት ነው
- ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ጥራትና ወጪ ቆጣቢ አገ/ት እንሰጣለን፡፡
- ስራችንን በታማኝነት እንፈጽማለን፡፡
- በጋራ እንማማራለን፡፡
- ውጤታችንም ሆነ ውድቀታችን የጋራችን ነው፡፡

## <u>አጠቃላይ ዓላማ፣</u>

ዞናችንና የዞናችን ህ/ሰብ ካለው በግብርና ላይ ከተመሠረተ ኢኮኖሚ ወደ እውቀትና መረጃ ታግዞ ኢኮኖሚ እና ህ/ሰብ ለመቀየት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዋናው መዘውሩ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ፈጣንና ቀልጣፋ በማድረግ መልካም አስተዳደርንና ዲሞክራሲን ማስፈን ነው፡፡

## የሥራ ሂደቱ ተግባርና ኃላፊነት

- በሥሩ ለሚገኙ ሴክተሩ መ/ቤቶች መለስተኛ የኢኮቴ መሠረተ ልማትና ዝርጋታ መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ሥልጠና ይሰጣል፣

- ብልሽት ለሚገጥማቸው የኢኮቴ መሣሪያዎች መለስተኛ ጥገና አገ/ት ይሰጣል፣
- Point to point የቪዲዮ ኮንፍራንስ፣ የዳታ፣ የኢሜይልና የኢንተርኔት አገ/ት ይሰጣል
- በየደረጃው ላሉ አካላት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል
- በሥሩ ለሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣

## *በሥራ ሂደቱ ፈፃሚዎች መካከል ያለ ግንኙነት*

እያንዳንዱ የሥራ ሂደቱ አባል ከጥናትና ከእቅድ ጀምሮ በዲዛይንና ስፔስፊኬሽን ዝግጅት በኔትወርክ ዝርጋታና ስልጠና እንዲሁም ለደንበኞች በሚሰጡ የኢኮቴ አገልግሎቶች በቪዲዮ ኮንፍራሲንግ በድጋፍና ምክር አገልግሎት እኩል ሁለት ንዑሣን ቲሞች አሉት

- የኔት ወርክና ሥልጠና ባለሙያ
- የጥገናና የምክር አገልግሎት ባለሙያ

## *የሥራ ሂደቱ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት*

- የዞኑ መንግስትና በየደረጃው ያሉ የመንግስት ተቋማት
- ህብረተሰቡ

**ባለ ድርሻ አካላት**

- የዞኑ መንግስት
- ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን
- ት/ት ሚኒስቴር
- ት/መ/ዘዴዎች
- ፌዴራል ኢኮቴ ኤጀንሲ
- አቅ/ግ/ሚኒስቴር

## *የሥራ ሂደቱ ከሌሎች ሥራ ሂደቶች ያለው ግንኙት፤*

የሥራ ሂደቱ ሌሎች የሥራ ሂደቶች የመረጃ ልውውጣቸውንና አጠቃላይ ሥራቸውን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቀልጣፋና ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማከናወን እንዲችሉ ፍላጐቶችን በማጥናትና ከየሥራ ሂደቱ የሚቀርቡ አገ/ት ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ ፣

- የኢኮቴ መ/ልማቶችን እንዲዘረጋ ያደርጋል፣
- ሁሉንም አገ/ት ከንድ ማዕከል እንዲያገኙ ያደርጋል
- ሌሎች የሥራ ሂደቶች ከአቅማቸው በላይ የሆነባቸውን /ከባድ/ ጥገና አገ/ት እንዲያገኙ ያደርጋል

## የሂደቱ የሰው ኃይል መረጃ

በአዲሱ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በዞን መምሪያ የኢኮቴ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት ሲሆን የተፈቀደው የሰው ኃይል 2 ባለሙያ ነው፡፡ ይህም አንድ አስተባባሪና አንድ ፈፃሚ የሚያካትት ነው፡፡